# የሥራ አስኪያጁ መልዕክት




ግብር እና ታክስ ለክልሉ ልማትና ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚያገለግል የገቢ አቅም ለመፍጠር እና ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍል እንዲኖር ለማድረግ ከመንግስት የወጪ ፕሮግራም በመስተጋብር የሚያገለግል የፊሲካል ፖሊሲ መሳሪያ ነው፡፡ የህብረተሰቡ የጋራ መገልገያ የሆኑትን መሰረተ ልማቶች እና የማሕበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለመገንባት እንዲሁም መልካም አስተዳደር ለማስፈን በአጠቃላይ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚውል የክልሉን መንግስት የወጪ ፍላጎት ለመሸፈን/ለመደገፍ የሚያስችል ገቢ ከህብረተሰቡ በግብር እና በታክስ መልክ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

በክልላችን ባለፉት በርካታ ዓመታት የገቢ አቅማችን የወጪ ፍላጎታችንን የመሸፈን አቅሙ በአማካይ ከ16 በመቶ እምብዛም ያልዘለለና በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ የልማትና የመደበኛ ወጪያችን በአብዛኛው የሚሸፈነው ከፌዴራል መንግስት በሚገኘው የድጎማ በጀት ነው፡፡ የክልሉ የገቢ አቅም እጅግ ዝቅተኛ እዲሆን ያደረጉት ሁለት ቁልፍ ችግሮች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱ በበርካታ የአሰራርና የስነምግባር ችግሮች የተተበተበና የመረጃ ሥርዓቱም እጅግ ደካማ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ህብረተሰቡ ግብር እና ታክስ ከሀገር ዕድገትና ህልውና ጋር አሰተሳስሮ የሚገነዘብበት ደረጃ ለይ ባለመድረሱ ሰፊ የግብር ስወራና ማጭበርበር የሚፈፀም በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ከክልሉ ህብረተሰብ የሚሰበሰበው ግብር እና ታክስ ለክልሉ ልማት በቂ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ትርጉም ያለው የገቢ አቅም ለመፍጠር የግብር ሰብሳቢ ተቋም የመፈጸምና የማስፈፀም አቅም በማጎልበት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በዘላቂነት ከመፍታት በተጨማሪ ሕብረተሰቡ በሕግ የተጣለበትን ግብር እና ታክስ የመክፈል ግዴታ በራስ ተነሳሽነትና በታማኝነት መወጣት የሚችልበት የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ ማድረስ ይጠይቃል፡፡

በክልሉ የታክስ አስተዳደር ተቋም በኩል የአገልግሎት አሰጣጡን ተገልጋይ ተኮር ለማድረግ፣የማስፈፀም አቅሙን ለማጎልበት እና ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ በራስ ተነሳሽነት ላይ ተመስርቶ በታማኝነት የሚፈለግበትን ግብር እና ታክስ የመክፈል ግዴታውን እንዲወጣ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች በመሰራት ላይ የሚገኝ ሲሆን ወደፊትም ተጠናክረው የሚቀጥሉ ተግባራት እንዳሉ ተቋሙ ይገነዘባል፡፡ በዚህ ረገድ ተቋሙ የተቋቋመበትን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት ማከናወን የሚጠበቅበትን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት የነበሩበት የአሰራር ችግሮችና የአፈፃፀም ደረጃዎች አንጥሮ በመለየት በነባሩ አሰራር የተስተዋለውን ኋላ ቀር፣ የተንዛዛና ግልፅነትና ተጠያቂነት የጎደለውን አሰራር ከስረ መሰረቱ በማስወገድ የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እና ስር ነቀል የአሰራር ለውጥና እመርታዊ የአፈፃፀም ውጤት ለማስመዝገብ ተቋሙ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት/ BPR / አካሂዷል፡፡

በዚህም ተቋሙ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ :-

- ጥራት ያለው ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት ወጪና ጊዜ ቆጣቢ የታክስ ሥርዓት ማስፈን፣
- የገቢ መሠረቱን በማስፋት ለክልሉ ልማት ትርጉም ያለው የገቢ አቅም መፍጠር ፣
- ፍትሃዊና ሚዛናዊ የታክስ ስርዓት ማስፈን፣
- የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ተራማጅና ተወዳዳሪ የታክስ ማዕቀፍ መቅረፅ እና
- ተገልጋዩ የግብር/የታክስ ግዴታውን በታማኝነትና በፍቃደኝነት እዲወጣ የሚያስችል ሁኔታዎችን መፍጠር ከጥናቱ የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው፡፡

የጥናቱ አፈፃፀም በአራት ደረጃዎች ተከፋፍሎ የተካሄደ ሲሆን፣

- በደረጃ አንድ የተቋሙ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት የሚጠብቋቸውን ውጤቶች መሰረት በማድረግ ከግብዓት እስከ ውጤት ያሉ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ እሴት በመፍጠር ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ሶስት ዋና የስራ ሂደቶችን የመለየት፣

  በተቋሙ የሚከናወኑ ከግብዓት እስከ ውጤት አንድ ላይ በማደራጀት ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት እሴት ለመፍጠር የሚያስችሉ ሦስት ዋና የሥራ ሂደቶች ተለይተው በክልሉ ስትሪንግ ኮሚቴ የፀደቁ እዲሁም በክልሉ አቅም ግንባታ እና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች አማካኝነት በዋና የስራ ሂደትነት ተጠንተው የቀረቡ ጥናቶችን መነሻ በማድረግ አራት ደጋፊ የስራ ሂደቶችን በመለየት ተቋሙ በሰባት ዋናና ደጋፊ የሥራ ሂደቶች በአዲስ መልክ እዲዋቀር ተደርጓል፡፡ የክልሉ የታክስ አስተዳደር ባለስልጣን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት የሚጠብቋቸውን ውጤቶች መሰረት በማድረግ የተለዩና በተቋሙ አፈጻጸም ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ የታመነባቸው የስራ ሂደቶች፡-

  1. የገቢ ማዕቀፍ ጥናት እና የታክስ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና ሥልጠና ዋና የሥራ ሂደት፣
  2. የግብር ከፋዮች ምዝገባ፣ የገቢ አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት፣
  3. የኢንተለጀንስና የታክስ ሕጎች ማስከበር ዋና የሥራ ሂደት፣

እንዲሁም በክልሉ ደረጃ በተመረጡ ቢሮዎች በዋና የስራ ሂደትነት የተጠኑና የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴ የሚደግፉ የሥራ ሂደቶች፦

1. የመረጃ ቴክኖሎጂ አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት፣
2. የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ክትትልና ግብረ መልስ ደጋፊ የሥራ ሂደት፣
3. የግዥ፣ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት፣
4. የሰው ሀብት ሥራ አመራር ደጋፊ የሥራ ሂደት፣

በአዲስ መልክ በመቅረጽ አገልግሎቱን በብቃት፣ በጥራትና በቀልጣፋ አሰራር ለመስጠት እንዲችል ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡

- በደረጃ ሁለት የስራ ሂደቶችን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት (Understanding AS IS) ከተቋሙ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶችና ችግሮች አንጻር የነባሩን አሰራር የአፈጻጸም ደረጃ (Performance Baseline) እና የተፈጠረውን የአፈጻጸም ክፍተት (Performance GAP) ከጊዜ፣ ከጥራትና ከወጪ አንጻር ለይቶ የመተንተን፡፡

- በደረጃ ሦስት በነባሩ አሰራር የተፈጠሩትን የአፈጻጸም ክፍተት ለመሙላት ተፈላጊ የግብ ስኬቶችን (Desired Outcomes) በመንደፍና በከፍተኛ ጥረት የሚደረስባቸው ግቦችን (Stretched Objectives) በመጣል ከጊዜ፣ከጥራት፣ከወጪና ከተደራሽነት አንፃር ለአፈጻጸም ድክመት መንስኤ የሆኑ ነባር አሰራሮችንና ታሳቢዎችን በማፋለስ፣ አዳዲስ ታሳቢዎችንና ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ የሪ-ዲዛይኒግ መርሆዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ ተመዝኖ በጥረት ተደራሽ ግቦችን ሊያሳኩ የሚችሉ አማራጭ የስራ ሂደቶችን በመቅረጽ እና ከተቀረጹት አዲስ የስራ ፍስት አማራጮች መካከል በብቃት መመዘኛ መስፈርቶች የአፈጻጸም እመርታ ሊያስገኝ የሚችል ተመራጭ የስራ ሂደት ዲዛይን የመለየት፡፡

- በደረጃ አራት አጠቃላይ የጥናት ስራው የሚቋጭበት ደረጃ እንደመሆኑ መጠን በተለያዩ የመምረጫ መስፈርቶች ተመዝኖ የተመረጠውን የስራ ፍሰት አማራጭ ዲዛይን የማደራጀት ሥራ የአገልግሎት አሰጣጣችን ለተገልጋዮች ተደራሽና ቀልጣፋ እዲሁም ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ ለተመረጠው የሥራ ፍሰት ዝርዝር ተግባራትንና ያላቸውን የስራ ስፋት የመለየት፣ ስራው የት መሰራት እዳለበት፣ ማን መስራት እዳለበት፣ በስንት ፈጻሚ ባለሙያ መከናወን እዳለበት እና የፈፃሚዎች ተፈላጊ ችሎታ በየአስተዳደር እርከኑ (ከክልል ማዕከል እስከ ወረዳና ከተማ አስተዳደር) በመለየት ለትግበራ የሚያመች ቅርጽ በማስያዝ በተቋሙ የሰው ኃይል ያልተመደበለት ሥራና ሥራ የሌለው የሰው ኃይል እንዳይኖር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለፈጻሚዎችና ለአስፈጻሚዎች የሚያገለግል የአሰራር ማንዋልና የቡድን ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ተቋሙ ከግንቦት10/2001ዓ.ም ጀምሮ በተመረጡ የዞኖች፣ የወረዳዎችና የከተማ የታክስ አስተዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሙከራ ትግበራ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ተቋሙ  በክልሉ የግብር እና የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ አፈጻጸም ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ዝግጅቱን አጠናቅቆ የሚገኝ ስለሆነ በተቋሙ ውስጥ ባሉት የስራ ሂደቶች የተመደቡ ሰራተኞች በተመደቡበት የስራ ሂደት የተደራጁ ሥራዎችን አጠቃላይ ባህሪና ምንነት መገንዘብ፣ ምክንያት የሚያበዙ ሳይሆኑ በራሳቸው የሚወስኑና የሚፈጽሙ ሆኖ መገኘት፣ የህግ አምላኪ ሳይሆኑ ለሚያጋጥሙ መሰናክሎች ተነጋግረው በጋራ መግባባት መንፈስ መፍትሄ የሚያመነጩ እንዲሁም ጠንካራ ራስን በራስ የመምራት ዲስፕሊንና ተገልጋይን ለማርካት ተነሳሽነት፣ ቁርጠኝነት፣ ታታሪነትና ታማኝነት ያላቸው ሆኖ መገኘት ከተቋሙ ሰራተኞች ይጠበቃል፡፡ ምክንያቱም በተቋሙ ተግባራት አደረጃጃት ላይ የተካሄደው መሰረታዊና ስርነቀል የሆነ ሳይንሳዊ ለውጥ በወረቀት ላይ የሰፈረና ግዑዝ በመሆኑ ወደ ውጤት ሊሸጋገር ሚችለው መላው የተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ከሁሉ አስቀድሞ የለውጡ ባለቤት ለመሆን የሚያስችላቸው የአስተሳሰብ ለውጥ በራሳቸው ላይ ሲያረጋግጡ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

የግብር ከፋዩ ህብረተሰብም የተቋማችን አደረጃጀት የተገልጋዮችን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችል ሁኔታ በአዲስ መልክ ተቀርፆ ተግባራ ለማድረግና የአፈጻጸም እምርታ ለማስመዝገብ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንደ መልካም ጅምር በመውሰድ ከተቋማችን ጋር በፍፁም መቀራረብና አጋርነት መንፈስ የተመሰረተ መልካም የስራ ግንኙነት ለመፍጠር እንዲያስችል በአፈጻጸማችን ላይ ግልጽና ሐቀኛ ግብረ መልስ በመስጠት የበኩሉን አውንታዊ ድርሻ እንዲወጣ እዲሁም የክልሉ ግብር ከፋይ ህብረተሰብ የሕግ የበላይነትን በማክበር፣ ለታክስ ህጎች ተገዥ በመሆን መክፈል የሚገባውን ግብር እና ታክስ በፈቃደኝነትና በታማኝነት በወቅቱ በመክፈል የዜግነት ግዴታውን በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል። መላው ህብረተሰብም የታክስ ስወራና ማጭበርበርን ለመከላከል የጥቆማ መረጃዎችን በመስጠት ከባለስልጣኑ መ/ቤት ጎን በመቆም ትብብር እንዲያደርግ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

**<u>የተቋሙ ራዕይ</u>** **<u>(Vision)</u>**፣

በክልሉ ዘመናዊ፣ፍትሃዊና ጤናማ የታክስ ስርዓት ሰፍኖ፣ የግብር ከፋዩ ህብረተሰብ የታክስ ህጎች ተገዢነት ባህል ዳብሮ ከኢኮኖሚው የሚመነጨው የገቢ አቅም ለክልሉ ልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ አስተማማኝ መሰረት ሆኖ ማየት፤

**<u>የተቋሙ ተልዕኮ</u>** **<u>(Mission)</u>**፣

- ለክልሉ ልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ አስተማማኝ የገቢ አቅም መፍጠር፣
- ለተራማጅ የኢኮኖሚ ልማት አጋዥና ጤናማ የታክስ ሥርዓት መመሥረት፣
- ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ አሰራር በመመስረት የተገልጋዮችን ፍላጎት ማርካት፣

**<u>የተቋሙ ዓላማ</u>** **<u>(Goal)</u>**፣

የተቋሙን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለመገንባትና የክልሉን የታክስ ሥርዓት ዘመናዊ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራም በብቃት በመተግበር እንዲሁም የግብር ከፋዩን ህብረተሰብ የታክስ ግዴታዎችን በፈቃደኝነትና በታማኝነት እንዲወጣ በማነሳሳትና በማጠናከር ከክልሉ ኢኮኖሚ የሚሰበሰበው የገቢ አቅም በተከታታይና በፍጥነት ማሳደግ፣

**<u>የተቋሙ እሴቶች</u>** **<u>(Values)</u>**፣

- ለተገልጋዮቻችን ከበሬታ በመስጠት በቅንነትና በትህትና ማገልገል መለያችን ነው!
- ቅሬታ አቅራቢዎች አጋሮቻችን ናቸው!
- የታክስ ውጤታማነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ መሠረታዊ ተልዕኳችን ነው!
- ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማስፈን የስራዎቻችን ጥራትና ማረጋገጫ ነው!
- ተገልጋዮቻችን የሕልውናችን መሰረቶች ናቸው!
- የመልካም ሥነ ምግባር እሴቶችን መላበስ ተቋማዊ ስብዕናችን ነው!
- በመማማርና በመደጋገፍ መልካም የሥራ ግንኙነት መመስረት የተቋማዊ ውጤታችን ምንጭ ነው!
- የመልካም አስተዳደር መርሆዎች መመሪያዎቻችን ናቸው!